*“የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።”*

*2ኛ ጢሞ 3፡16-17*




ቦስተን የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የሥነ-ጽሑፍ አገልግሎት
በሁለት ወር አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ የሚቀርብ መንፈሳዊ ጋዜጣ

# በውስጥ ገጾች

- **ዕርሰ አንቀጽ፤**
  - **እግዚአብሔር በማወቅ እንደግ**

    *እግዚአብሔርን በማወቅ እራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ እለት እለት እንድናድግ ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ ግድ ይለናል።*

- ***እንግዳችን፤***

  እግዚአብሔርንም ፈልጌው ስላልተቀበለኝ በራሴም *መለወጥ ስላልቻልኩ፤ በዚህ ዓይነት ህይወት መቀጠል ደግሞ ስለማልፈልግ መፍትሄው ራሴን ማጥፋት መሆኑን ወሰንኩ።*

- **የትምህርት ዓምድ፤**
  - *እንግዲህ የእግዚአብሔር ዓላማ ነፃ ባወጣው ህዝብ የቅድስናውን ባህሪ መግለጥ ነው። ወደ አዲስ ኪዳንም ስንመጣ የክርስቶስ ኢየሱስ አካል በሆነች ቤተክርስቲያን ወይም ዳግመኛ በተወሰዱ ቅዱሳን እግዚአብሔር በልጁ የራሱን ባህሪ እንደገለጠ ሁሉ በእኛ ደግሞ የክብሩን መንጸባረቅና የባህሪው ምሣሌ የሆነውን የኢየሱስን ክርስቶስን ባህሪ መግለጥ የእግዚአብሔር ዋነኛ ዓላማ ነው።*

- ትዳር ምንድን ነው?
  - *በቃ አዳምን ሲፈጥረው አንድ አድርጎ እንደሰራውና ጌታ እራሱ በመለኮታዊ ኃይሉ ሔዋንን አውጥቶ እስኪሰጠው ድረስ ከአዳም ለይተን ማየት እስከማንችል አንድ እንደነበሩ ሁሉ አሁንም ትዳር ውስጥ ልክ እንዲሁ መለየት የማይቻል አንድነት ወይንም ውህደት አለ።*

በቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የምታምን የክርስቶስ ኢየሱስን የማዳን ወንጌል ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የምታሰራጭ ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህም ጋዜጣ ወንጌልን ከምታሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ ሲሆን በቤተ ክርስቲያን የሥነ-ጽሁፍ አገልግሎት አባላት እየተዘጋጀ በየሁለት ወር አንድ ጊዜ ይቀርባል።

**የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ**
**ፓስተር ምሕረቱ ሌጂቦ**

Email: Meheretu2614@yahoo.com
Telephone: 617-792-5764

ዋና አዘጋጅ ..........ሄኖክ ተሾመ
ምክትል አዘጋጅ........ ሐብታሙ አስረስ
የውብዳር ፍሰሐ
ኮምፒዩተር ጽሑፍ... . ትርሲት ጥላሁን
የፊት ገጽ ዲዛይነር...ዘነበ ምትኩ

ለቀጣዩ እትም ይረዳ ዘንድ የእናንተ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ስላለው በሚቀጥለው አድራሻ ያላችሁን አስተያየትና ጥያቄ ላኩልን። አድራሻ:

Ethiopian Evangelical Church in Boston
88 Tremont Street
Boston, MA 02108
Tel. 617-816-8827
E-mail: Henokekka@yahoo.com



የእግዚአብሔር አምላካችን ቃል ሕያው ነው አይለወጥም!

# ርዕሰ አንቀጽ፤

## እግዚአብሔር በማወቅ  እንደግ፤

መጽሐፍ ቅዱሳችን መልእክቱን ሲጀምር ስለ እግዚአብሔር መኖር ማስረጃ በማቅረብ አይደለም፤ ከዚያ ይልቅ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ይለናል። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን ይህ ጅማሬ እና ፍጻሜ የሌለው አምላክ እንዲህ ወይም እንዲያ ተብሎ ለመግለጥ ቃላት የሚጠፉለት እራሱን በተለያየ መንገድ ገልጧል፤ እራሱን ከገለጠበት መንገድ አንዱ በፍጥረቱ ነው ምድርና ሞላዋ ሰማየ ሰማያት ክዋክብት ፀሐይ ጨረቃ የሰው ልጅ ሰንቱ ይገለጣል እነዚህን ስናይ እግዚአብሔርን እናያለን፤ ሌላውና ትልቁ እግዚአብሔር እራሱን የገለጠበት መንገድ ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ ወደዚ ች ምድር በመምጣት በሰው ልጆች መካከል በፍቅርና በሥልጣን በመመላለስ እግዚአብሔርን ያየው አንድስ እንኳን የለም ነገር ግን በእቅፉ ያለው አንድያ ልጁ ተረከው (ገለጠው) ይላል፤ እንዲሁም በሌላ ክፍል ላይ .........በዕብ.1፤3 እርሱ የክብሩ መንጸባረቂያና የባሕሪው ምሳሌ ነው ይላል። ታድያ በልጁ አማካኝነት እራሱን የገለጠው ጌታ ቅዱሳን ሁሉ እርሱን በማወቅ እንድናድግ በብርቱ ይፈልጋል። በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ ዳግመኛ ከመወለድ ጀምሮ በሕይወታችን የሚታይ ክርስቲያናዊ ባሕሪ ወይም ቃሉን የሚገልጥ ሕይወት በኑሯችን ካለ ያ እግዚአብሔርን በማወቃችን ምክንያት የመጣ ለውጥ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን ከዳንን በኋላ ለሞተው መንፈሳችን ሕይወትን በመስጠት እግዚአብሔርን እንድናውቅ አድርጎናል። አሁንም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ቃሉን ለመንፈሳችን እየገለጠ የበለጠ እግዚአብሔርን አውቀነው እንደሚገባ በጽድቅ እንድንመላለስ ማድረግ ነው። እግዚአብሔርን ባወቅነው መጠን እንታመነዋለን በተገለጠልን ልክ እንገዛለታለን እንፈራዋለን ደግሞም እናመልከዋለን፤ እንግዲህ እግዚአብሔርን በማወቅ እራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ እለት እለት እንድናድግ ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ ግድ ይለናል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን የምናውቅበትን እምነት ካወቅነው በኋላ ደግሞ የምንገዛበትን ፀጋ የምናገኝበት መሠረታዊ ምንጭ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነውና ነፍሳችንን በአምላካችን ቃል ለመመገብ እንወስን እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ትኩረታችን እና አላማችን ይሁን።

የቤተ ክርስቲያኒቱ መልዕክት

ትዕ



# የቤተሰብ ዓምድ

## ትዳር ምንድነው?

*ካለፈው የቀጠለ፤........ባለፈው ዕትም እግዚአብሔር አዳምን ለብቻው ፈጥሮት ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ያለው ተሣስቶ ነው? ከጎኑ የወሰዳትን አጥንት ሴት አደርጐ የሰራት ስህተቱን ለማስተካከል ነው?ብለን ነበር ያቆምነው ። ቀጣዩን እነሆ...*

*እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በአዳምና በሔዋን መካከል ያለውን አንድነት (በትዳር ውስጥ ያስቀመጠውን ፍጹም የሆነ ውህደት) ሊያሳይ ፈልጎ እንጂ ተሳስቶ አይደለም። አንድ እውነት ልንገራችሁ አዳምን ሲፈጥረው በእርሱ ውስጥ ሔዋንን ሰርቶ ጨርሷል፤ እንዴት ብትሉ ሔዋንን ለመስራት ሌላ አፈር ሲጠቀም አናየውም እንደገና በሔዋን ውስጥ የህይወት እስትንፋስ እፍ አለባት የሚል ተጽፎ አናገኝም ሁሉም የተጠናቀቀው በአዳም ውስጥ ነው፣ በቃ እግዚአብሔር አዳምን ሊሰራው ለእሱ ሙሉ ሰው ነው፤ ምክንያቱም በአዳም ውስጥ ሄዋንን ስለሚያይ፤ ማስረጃ ልስጣችሁ እግዚአብሔር ሰውን ሳይፈጥረው አስቀድሞ ሊሰራ ያለው ነገር በምእራፍ አንድ ላይ ተናግሮአል፤ እንዲህ ሲል ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር ይልና ሰውን በመልኩ ፈጠረ ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ይላል ዘፍ 1፡26-27 ልብ በሉ እግዚአብሔር ይህንን ሲናገር ሰውን ገና አልፈጠረውም ነገር ግን ሊሰራ ያለውን በግልጽ አስቀድሞ ሲናገር ታያላችሁ የሚገርማችሁ ምእራፍ ሁለት ላይ ስትመጡ ነው አዳምን ከምድር አፈር አበጀው ካለ በኋላ እንደገና ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ብሎ ሄዋንን ከአዳም ጎን በወሰዳት አጥንት ሰርቶ ሲያመጣት የምታዩት ዘፍ 2፡21-22 ይህንን ስንመለከት እግዚአብሔር በፍጹም የማይሳሳት ሁሉን የሚያውቅ አምላክ መሆኑን ያረጋግጥልናል።*

*አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እግዚአብሔር ሔዋንን ከአዳም ውስጥ ባያወጣት ሁለቱም መለየት ይቻል ነበርን? አዳምንስ ወደእኛ አምጥቶት ስንት ሰው ነው ቢለን ሁላችንም አንድ እንለው ነበር አይደል ምክንያቱም ለእኛ ሔዋን ስለማትታየን፣ ወገኖቼ ይህንን ልዩነት የሌለው አንድነት ሊያሳየን ሔዋንን በአዳም ውስጥ ሰውሮ ፈጥሯታል። በትዳር ውስጥ እንዲህ ልዩነት የሌለን አካል መሆናችን እንዲገባን ይህንን አድርጓል፤ በቃሉ ሰው እናቱንና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ይል አይደል። ዘፍ 2፡24 በቃ አዳምን ሲፈጥረው አንድ አድርጎ እንደሰራውና ጌታ እራሱ በመለኮታዊ ኃይሉ ሔዋንን አውጥቶ እስኪሰጠው ድረስ ከአዳም ለይተን ማየት እስከማንችል አንድ እንደነበሩ ሁሉ አሁንም ትዳር ውስጥ ልክ እንዲሁ መለየት የማይቻል አንድነት ወይንም ውህደት አለ። ስለዚህ ወደድንም ጠላንም ይህ እውነት ካልገባን ትዳር ትርጉም ሊሰጠን አይችልም።*

*እንደገና ነገሩ የበለጠ ግልጽ እንዲሆንልን ዘፍ 2፡23 እንመልከት፤ እዚህ ክፍል ላይ እግዚአብሔር በአዳም ከባድ እንቅልፍ ጥሎበት ከጎኑ በወሰዳት አጥንት ሔዋንን ሰርቶ ሲያመጣት አዳም እንዲህ አለ፤ ይህቺ አጥንት ከአጥንቴ ሥጋዋም ከሥጋዬ ነው። ልብ በሉ አዳም በንግግሩ ውስጥ አንዳች ጥርጣሬ የለውም እግዚአብሔርም ምንም ሲናገር አታዩትም። አዳም ግን የራሱ አካል ለመሆኗ እርግጠኛ ነው፤ እግዚአብሔር እራሱ ቼክ ሲያደርገው ነው የምናየው። ምክንያቱም አዳም ሔዋንን ከእሱ ስትወጣ በፍጹም አላያትም በከባድ እንቅልፍ ውስጥ ነበር። ግን የሚደንቀው ያለ ምንም ግራ መጋባት የእኔ አካል ነች አለ። ጌታም አላማው ሔዋን አካሉ መሆኗል እንዲያውቅ ነበር። አሁንም አንድ ነገር አሰብኩ፤ ሔዋን እንደ አዳም ከሌላ አፈር ተሰርታ ቢሆን ኖሮ አልኩኝ በልቤ ጌታ ነበር የሚያስተዋውቃቸው፤ ምክንያቱም አካሉ አይደለችም፤ ይዟትም እንደመጣ አዳምን ጠርቶት ሚስት አመጣውልህ ተዋወቃት ይለው ነበር፤ ግን ከራሱ ስለወጣች አዳም ማንም ሳያስተዋውቀው ከእኔ ነች ደግሞም የእኔ ነች አለ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን። ይህንን ድንቅ አንድነት ለሁላችንም በትዳራችን ውስጥ ያብራልን።*

*ወገኖቼ ጋብቻ ፍጹም በሆነ አንድነት ፍቅርና መከባበር በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ፀንቶ የሚኖርበት ጣፋጭ ህይወት ነው። ብዙ ሰዎች ግን በተሳሳተ አላማ ላይ ትዳራቸውን እየመሰረቱ ጋብቻን የሲኦል ያህል እያማረሩ ሲኖሩ ይታያሉ፤ በጥቅማ ጥቅም ላይ የሚመሰረት ትዳር የትዳር ዓላማን የሳተ በመሆኑ የራስ ያልሆነ አካል ለማዋሃድ መሞከር ወይንም ድመትና አይጥን አብሮ ለማኖር የመታገል ያህል ነው። ይህ ደግሞ በፍጹም የማይቻል ሲሆን ከዚህም የተነሳ በየትኛውም ነገር መግባባት አንድ መሆንን አይችሉም አንዱ የበላይ አንዱ የበታች አንዱ ባሪያ አንዱ ጌታ በመሆን የሚኖሩባቸው ትዳሮች ሞልተዋል፤ የሚገርማችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ለተገዛለት ነገር ለዚያ ባሪያ ነው ይላል፤ በቃ ሳይወዱ የግድ ትዳር ባርነት ሆኖባቸው የሚኖሩ ሰዎች የትዬሌሌ ናቸው። አዳም ግን ሔዋንን ሲወዳት የራሱ አካል እንደሆነች ገብቶት እንጂ ቤት እንድታጸዳ ሞቅ ሞቅ እንድታደርግ ወይም ዘመኑ ክፉ ስለሆነ ማምለጫ እንድትሆነው አስቦ አልነበረም፤ አንድ ነገር ግን ይገባኛል በጋብቻ ውስጥ ቤት መጥረግ፤ አልጋ ማንጠፍ፤ ቤትን ሞቅ ሞቅ ማድረግ አለ ያ የማይቀር እውነት ነው ከዚህም ሌላ በኃጢያት ላለመውደቅ ለሌላም ለሌላም ይረዳል፤ ግን ዋናው ቁም ነገሩ ምንድ ነው ቢባል ትዳር በነዚህ መሻቶች ላይ ከተመሰረተ ጥፋቱ አደገኛ ነው፤ የትዳር መሠረቱ ከላይ እንደተጠቀሰው በእግዚአብሔር ፈቃድና በእውነተኛ ፍቅር ላይ መሆን አለበት።*

*መጽሐፍ ቅዱስ ሚስት ለባሏ እንድትገዛ ባል ደግሞ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደደ ሚስቱን እንዲወድ ያዛል ኤፌ 5፡21-23 ቃሉ ግልጽ አድርጎ በባልና በሚስት መካከል ስላለው ግንኙነት ይናገራል፤ ሚስት ለጌታ በፍቅር በታማኝነት እንደምትገዛ ለባሏም በፍቅር በታማኝነት እንድትገዛ መመሪያ ይሰጣል፤ ባል ደግሞ እንደገዛ ሥጋው ሚስቱን እንዲወድ ሚስቱን የሚወድ እራሱን ይወዳል ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ የለምና እያለ ምን ያህል በአንድነት እና በእውነተኛ ፍቅር ላይ ተመስርተን መኖር እንዳለብን አስረግጦ ይናገራል፤ ከዚህ ክፍል ላይ የሚደንቀኝ ቃል ቢኖር ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ የሚለው ሃሳብ ነው፤ ሚስት ለባሏ መገዛት አለባት ይልና ለባል ግን ጠንከር ያለ ትእዛዝ ያስተላልፋል፤ እራሱን አሳልፎ እንዲሰጥ ምክንያቱም ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እራሱን አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ ነው የወደዳት፤ ስለዚህ ለባል የተሰጠው ትእዛዝ ጠንከር ያለ ነው።*

*ይህንን ሳይ በጣም የሚገርመኝ ፤ ለሚስት የተሰጠው ለባሏ የመገዛት ለባል የተሰጠው ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቱን የመውደድ ትእዛዞች በሙሉ የፍቅር ህግ መሆናቸው ነው፣ ይህ እጅግ ያስደንቀኛል፤ ክርስትና እራሱ የፍቅር ህይወት አይደል ትዳርማ እንዴታ ትልቅ የፍቅር ተቋም ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር በቃሉ ትዳር ምን ያህል ክቡር እንደሆነ ሊያሳየን እንደሞከረ ታያላችሁ ታዲያ ወገኖቼ ጋብቻ ስናስብ የምናገባትን ሴት ወይንስ ከበስተጀርባ ያለውን ጥቅማ ጥቅም ማንን ነው የምንወደው ይህንን ለእናንተ ተውኩት።*

*እንኪያስ "ትዳር ማለት ምንድ ነው ከላይ እንዳልኳችሁ በዚህ ርእስ ብዙ ማለት ቢቻልም በአጭሩ ለመግለጽ ትዳር ማለት አንድ ወንድና አንድ ሴት በእግዚአብሔር ፈቃድና በእውነተኛ ፍቅር ላይ ተመስርተው የሚኖሩት፤ እግዚአብሔር ለክብሩ መገለጫ እና*

ለዓላማው የፈጠረው፤ ፍቅር ሰላም ደስታ ፍጹም የሆነ አንድነትና መከባበር ያለበት ደግሞም የወደፊቱን የመንግስተ ሰማያት ኑሮ ማለትም የቤተክርስቲያንንና የክርስቶስን ፍጹም የሆነ የፍቅር ግንኙነት የምናይበት ምሳሌያዊ የሆነ ክቡር ህይወት ነው።” ከዚህ መረዳት ውጪ በሌሎች ተራና ድብቅ በሆኑ መሻቶች ላይ የሚመሰረቱ ጋብቻዎች በሙሉ የችግር አረንቋ ሆነው እያየን ነው። በጠማማ አላማ ትዳርን መሰርተን በሚፈጠሩብን የተለያዩ ችግሮች ግራ ሲገባን ሰላም ደስታ ሰናጣ ጌታን ልናማርር አንችልም ምክንያቱም በእራሳችን ፈቃድ ላይ ለመሰረትነው ትዳር ሃላፊው እራሳችን ነን በእርሱ ፈቃድ ላይ ላልተመሰረቱ ጋብቻዎች ጌታ ተጠያቂ አይደለም። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ከፍተኛ ችግር በትዳራችን ውስጥ ሲፈጠር ጋብቻችንን ለማፍረስ እንወስናለን፤ ይህ ደግሞ ሁለተኛ ጥፋት ነው፤ በእግዚአብሔር ፈቃድና በእውነተኛ ፍቅር ላይ ሳይሆን በሌሎች ነገሮች ላይ ጋብቻችንን መሰርተን በብዙ ሃዘንና ስቃይ ውስጥ ያለን ብዙ ወገኖች ለመኖራችን ግልጽ ነው በምድር ላይ ስንኖር ህይወት አንዴ ናት ደግመን አንፈጠርም ስለዚህ ጋብቻ ደግሞ የእድሜ ልክ ጉዳይ ነው፤ እንዲህ እንደ ቀላል እያየን ሰላምና ረፍትን ሊሰጡ በማይችሉ ቁሳዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ትዳራችን መሰርተን ለሰይጣን የተከፈተ በር አንስጠው፤ ጋብቻችን ውስጥ ክፍተት ካለ ሰይጣን ያሻውን ለማድረግ እድል ያገኛል ይህ ደግሞ ትልቅ አደጋ ነው፣ ስለዚህ ተጠንቅቀን በጌታ ፈቃድና በእውነተኛ ፍቅር ላይ ጎጆአችንን እንቀልስ።

በነገራችን ላይ አንዳንድ ሰዎች በእርግጥ ይህ አንተ የምትለው ፍጹም የተባረከ ትዳር በምድር ላይ አለ ወይ ይሉ ይሆናል ይህ ጥያቄ ሊሆንብን አይገባም ማወቅ ያለብን ግን እግዚአብሔር ትዳርን የመሰረተበት ዓላማው ወይም ሃሳቡ ይህ መሆኑ ነው።

ውድ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች እንግዲህ ጋብቻን ስናስብ እግዚአብሔር ለትዳር ባለው የተቀደሰ ዓላማና ውበቱ ካልሆነ ትልቅ ስህተት ውስጥ እንዳለን ልናውቅ ይገባል፤ ስለዚህ በውስጡ ያሉትን ጥቅማጥቅሞች ብቻ አስበን በድብቅ ዓላማ ከገባንበት የህይወት ዘመናችን እጅግ መራር ከመሆኑ ባሻገር ፍጻሜያችን አያምርም በደህንነታችን ላይ ሳይቀር ችግር ሊፈጥብን ይችላል፤ ይህንን እውነት አስተውለን ጌታም በትዳር ውስጥ ያስቀመጠውን ፍጹም የሆነ ደስታ ለማግኘት ጋብቻችንን በተቀደሰ ዓላማ ላይ እንመስርት፤ የእግዚአብሔር እቅድ በጋብቻ ውስጥ የሚገኘውን ደስታ ሁሉ በሰላምና በፍቅር በአንድነት እንድንቋደስና በዘመናችን እንደ ዳዊት የጌታን የልቡን ሃሳብ አገልግለን እንድናልፍ ነው።

ውገኖቼ አንድ ነገር እናስተውል በእርግጥ በእግዚአብሔር ፈቃድና በእውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሰረ ጋብቻዎች በቤተክርስቲያን ሲበዙ እውነተኛ ሰዎች ይበዛሉ፤ ይህ ደግሞ ለቤተክርስቲያን ትልቅ እረፍት ነው። እንደ ትልቅም ስኬት ይቆጠራል ለምን ቢባል **መልካም ቤተሰብ ማለት እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ከሚሰጣቸው ትልልቅ ስጦታዎች ውስጥ ዋነኛውን አንዱ ነው ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ በሙላት በውስጡ ስላለ፤** ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው በምእራፍ አምስት መልእክቱ ላይ ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ ባሎችም ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደደ ሚስቶቻችሁን ውደዱ ይልና ወረድ ብሎ ይህ ሚስጥር ታላቅ ነው፤ እኔ ግን ይህንን ስለክርስቶስ እና ስለቤተክርስቲያን እላለው ይላል ኤፌ 5፥21-32 እንግዲህ አስተውሎ ይህ ሚስጥር ታላቅ ነው ካልን ምን ያህል የከበረ ነገር ጌታ በትዳር ውስጥ እንዳስቀመጠ ታያላችሁ ትዳር በቀጥታ ከቤተክርስቲያን በእጅጉን የተቆራኙ እግዚአብሔርን ታላቅ ነገር በውስጡ ያኖረበት ክብር ህይወት ነው፤ ደግሞም ቤተክርስቲያንና ትዳር ሊለያዩ የማይችሉ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፤ ወዳጆቼ ይህ ብርቱ ሚስጥር በእኛ እንዲከናወን ከተፈጠርን እንዲያው እንንቃ፤ ቃሉም እኮ እንዲህ ይላል መልካሙን ሥራ ለማድግግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን ኤፌ 2፥10 እነዚህ እውነተኛ ትዳሮች ጌታ የሚመሰርታቸው ቃሉን እንደምናየው ለዓላማው ነው፤ እግዚአብሔር ጋብቻን ሰጥቶ በምድር እንድንኖር እድሜን ሲጨምርልን ለእርሱ ኖረን እንድናልፍ ነው ምክንያቱም የተፈጠርነው መልካሙን ሥራ ለማድረግ ነው ካለ ጌታ የፈጠረን ለዓላማው እንደሆነ ያሳያል፤ ስለዚህ ትዳር ሲሰጠን ልባችን በትዳራችን ላይ እንዲወድቅ ሳይሆን ለዓላማው ማስፈጸሚያ ነው ይህ ማለት መልካም ቤተሰብ ስለ መልካም ሥራ ወይንም ለወንጌል ይኖራል ማለት ነው ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፤ ታዲያ በእርሱ ፈቃድ ትዳርን ሲሰጠን በውስጡ ያሉትን የበዙ ደስታ ሰላም እያጣጣምን ለተፈጠርንለት ለመልካሙ ሥራ (ለወንጌል) መኖር መቻል አለብን፤ ስለዚህ ትዳርን ስናስብ አላማችን ቁሳቁስ ሳይሆን እግዚአብሔር ትዳር ለሰው ልጆች በሰጠበት የተቀደሰ ዓላማ ላይ መሆን አለበት፤ ይህ ሲሆን ጌታ በትዳር ውስጥ ያሉትን በረከት የተፈጠርንለት ዓላማ በህይወታችን እንዲፈጸም ያደርጋል። ከዚህም የተነሳ በጋብቻችን ውስጥ ትልቅ ስኬት ይሰጠናል ለምን ብትሉ እድሜ ሲጨመርልን ልባችን በመደረግ በሚያልፍ ነገር ላይ እንዲወድቅ ሳይሆን ልጁ የሞተለትን የወንጌል ሥራ እንድናሮጥለት ነው፤ በቃ ይህ እግዚአብሔር ትዳርን ሲመሰርት በውስጡ ያስቀመጠው ዘላለማዊ ዓላማው ነው፤ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።

በመጨረሻም ሳልገልጸው የማላልፈው አንድ እውነት አለኝ፤ እርሱም በእግዚአብሔር ፈቃድና በእውነተኛ ፍቅር ላይ በተመሰረቱ ትዳሮች መካከል ምንም ችግር አይፈጠርም ወይምን ነገር ሁሉ አልጋ በአልጋ ነው ማለቴ እንዳልሆነ ይታወቅ፤ ምንም አይነት ችግር ቢፈጠር የጌታ ጣት በቤታቸው ስላለና መሠረቱ እውነተኛ ፍቅር ስለሆነ ችግሮች እየተወገዱ እስከፍጻሜ የመሄድ ጉልበት አላቸው፤ ይህ እውነት ግልጽ ሊሆንልን ይገባል፤ ለማጠቃለል ያህል እግዚአብሔር ለትዳር ባለው የከበረ ሃሳብ ላይ የተመሰረቱ ትዳሮች ለቤተክርስቲያን ለሀገር ጥሩ ዜጋን ያፈራሉ፤ መልካም ቤተሰብ ሲመሰረት ጥሩ ቤተክርስቲያን ትኖራለች ማለት ነው፤

እንግዲህ ትዳርን ስናስብ እንዲህ አስፍተን ልናይ ይገባል፤ የአንድ ሰው ትዳር መቃናት ወይንም መልካም ቤተሰብ መፈጠር ከእሱ አልፎ ቤተክርስቲያንንና አገርን ይጠቅማል ትልቁና ዋናው ቁም ነገር ደግሞ ክርስቶስ ኢየሱስ እስከ መስቀል ሞት ዋጋ የከፈለለት የሰው ልጆችን ከዘላለም ሞት የማዳን ሥራ ለማሮጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፤ ሰላማዊ ቤተሰብ ለቤተክርስቲያን ሰላም ይሰጣል፤ ሰላም የሌለው ቤተሰብ ለቤተክርስቲያን ሰላም አይሰጥም፤ ልል የፈለኩት ግልጽ ይመስለኛል እናንተ ብዙ ልትሉ ትችላላችሁ የቤተክርስቲያን መሪዎች በጋብቻ ችግር ምክንያት ወደ እነርሱ በሚመጡ ሰዎች እንዴት ባለ ችግር ውስጥ እንዳሉ የአደባባይ ሚስጥር ነው፤ ካለማጋነን ለወንጌል እንኳ ሳይቀር ምን ያህል እንቅፋት እንደሆነ ታውቃላችሁ ከዚህ በላይ አልሄድም፤ በዚህ አቅጣጫ ብቻ ብዙ መጻፍ ይቻላል እኔ ግን በዚህ አጭር ጹሁፌ በእግዚአብሔር ፈቃድና በእውነተኛ ፈቃድ ላይ የተመሰረቱ ትዳሮች ለሁሉም መልካም ናቸው፤ ጥቅማቸውም ሰፊ ነው እላለሁ።

በሄኖክ ተሾመ

# እንግዳችን

የዛሬ እንግዳችን ወንድም ለቤዛ ዓለሙ ይባላሉ፤ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ናቸው፤ ኑሯቸው በአሜሪካ ሲሆን በቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በሽምግልና፤ በማህበራዊ አገልግሎት፤ በሕንፃ ግዥ ኮሚቴና በሌሎችም የአገልግሎት ዘርፎች አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ ስለእርሳቸው ጌታን እናመሰግናለን። ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት እና ወደ ጌታም ከመጡም በኋላ ለብዙዎቻችን ትምህርትና መጽናናት ሊሆን የሚችል የሕይወት ምስክርነት አላቸው። ይህን እንዲያካፍሉን በጠየቅናቸው ጊዜ በደስታ ጥያቄአችንን ተቀብለው እንዲህ አሉን ጌታ ያደረገልኝን በምን መንገድ ለሕዝብ ልናገረው እያልኩ አስብ ነበር ባገኘሁት አጋጣሚም ለብዙዎች ተናግሬያለው እንግዲህ ይህ የጌታ ጊዜ ነው አሉ። እኝህ ወንድም በምድራዊ ሕይወት ስኬታማ መሆን የውስጥ ሰላምና እረፍት አይሰጥም ሰላም እና እረፍት በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው ይሉናል።

እውነት............ ወንድም ለቤዛ ጥሪያችንን አክብረው ስለመጡ ጌታ ይባርኮት፤

ወንድም ለቤዛ....አሜን እናንተም ይህንን እድል ስለሰጣችሁኝ ጌታ ይባርካችሁ፤

እውነት ........... በቅድሚያ ወደ ጌታ ከመምጣትዎ በፊት ስለነበርዎት ሕይወት ቢገልጹልን ?

ወንድም ለቤዛ .... ዝርዝር የህይወት ምስክርነቴን ከመስጠቴ በፊት ለአንባብያን ይረዳ ዘንድ የልጅነት ህይወቴን በአጭሩ ብገልጽ ደስ ይለኛል። የልጅነት እድሜዬን ያሳለፍኩት ከቤተሰቦቼ ጋር ነው ቤተሰቦቼ በጥሩ ሥነ ምግባር ልጆቻቸውን ለማሳደግ እጅግ የሚጥሩ በትምህርታችን ጥሩ ውጤት እንድናመጣና ጥሩ ደረጃ ላይ እንድንደርስ ዘወትር የሚመኙ ነበሩ በዚህም በአካባቢው ነዋሪ ዘንድ ሁችንም በጥሩ ሥነ ምግባራችን ለትምህርታችን በምንሰጠው ትኩረት የምንታወቅ ነበርን።

በራሴ የዚህን ዓለም ህይወት መኖር የጀመርኩት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ጨርሼ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስገባ ነበር ይህ ለእኔ ሕይወት አዲስ ምእራፍ ነበር ። በዚህ ወጣህ በዚና ገባህ የሚለኝ የለም ሁሉን ነገር በራሴ ውሳኔ ሌሎች የሚያደርጉትንም እያየሁ መኖር ጀመርኩ።

የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ሆኜ ትምህርቱም ፋታ ስላልሰጠኝ ኑሮዬ ክፍል ውስጥ ማማር ፤ላይበረራ መሄድ፤ ማጥንት፤ መተኛት ነበር። በዓመቱ መጨረሻ ለክረምቱ እረፍት ትምህርት ቤት ሲዘጋ የክረምት ሥራ አገኘሁ ይህ በጣም ደስ አሰኘኝ ሥራው ላይ የተመደብነው እዚያው ዩኒቨርሲቲ ከተገናኘሁት ጓደኛዬ ጋር ነበር እርሱ ወደ ዩኒቨርሲቲ ከመግባቱ በፊት በመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ ለአንድ ዓመት የሠራና ኑሮንም በመጠኑ የተለማመደ ነበር፤ ሥራ ስንጀምር ምንም ገንዘብ ስላልነበረን እርሱ ከደመወዛችን የሚቀነስ ብድር እንጠይቅ አለኝ ጠየቅን ሰጡን ማታ ማታ ከሥራ መልስ እራታችንን ከበላን በኋላ ድሮ ቲቪ ማየት የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወት ነበር ሥራችን አሁን ወደ አራት ኪሎ ወረድ ብሎ ግሮሰሪ ውስጥ አልኮል መጠጣት ተጀመረ እኔ ልምዱ ስላልነበረኝ በለስላሳ እያደባለቅሁ መቀማመስ ጀመርኩ እያደር እየለመድኩት የለስላሳው መጠን እየነቀነሰ የአልኮሉ መጠን እየጨመረ እኔም መጠጧን ስቀምስ ድፍረቴ እየጨመረ ጨዋታውም እየጣመኝ መጣ ወደዚያ ሰፈር ጐራ ሳልል ማደር ቅር ቅር ይለኝ ጀመረ።

በዚህ መልክ የተጀመረው የኃጢያት ልምምድ ዘርፉ እየበዛ ሄደ ትምህርቱም አለቀ ሥራ ተጀመረ ህይወቴ ግን ምንም ሊለወጥ ሊሻሻል አልቻለም።

በዚህ ሁሉ የተመሰቃቀለ ሕይወት ሂደት ውስጥ ደግሞ በሥራ ቦታዬ የሚሰጠኝን ኃላፊነት ለመወጣት በማደርገው ጥረት የደረጃ እድገትና የደመወዝ ጭማሪ እያገኘሁ በከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት ላይ የመሥራት እድል ባገኝም የመጠጥ ሱሰኛ ስለሆንኩ ሥራዬን በአግባቡ መወጣት አልቻልኩም ከፍተኛ የገንዘብ አባካኝ ስለሆንኩ ደመወዜ ስለማይበቃይ የማይገባኝን ጥቅም ለማግኘትም አልተመለሰኩም።

ከሥራ ሰወጣ ዘወትር መጠጣት ነበረብኝ የምገባው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነው፤ ባለቤቴን ልጆቼን ለማየት እንኳን እድል አልነበረኝም፤ በማግስቱ ጠዋት ስካሬ ሳይለቀኝ ራሴን እያመመኝ እንቅልፌን ሳልጨርስ ወደ ሥራ እገባለሁ በዚህ ዓይነት ቢያንስ ለአሥራ አምስት ዓመት ኖርኩ፤ በዚህ ጊዜ

ውስጥ አንድም ቀን እውነተኛ ደስተኛ ተሰምቶኝ አያውቅም የእኔ እውነተኛ ደስታ መጠጥ ጠጥቼ ራሴን ስስትና የማደርገውን ነገር በማላውቅበት ሰዓት ነው፤ ይህንንም ስለምናፍቅ ነው ቶሎ ወደመጠጡ የምሮጠው ራሴን መቆጣጠር መግዛት ብፈልግም በፍጹም አልችልም፤ በተደጋጋሚ ከፍተኛ የሆነ የመኪና አደጋ ደርሶብኛል፤ ከባድ ጉዳት ግን ደርሶብኝ አያውቅም ሰዎች ሲያዩኝ ሁልጊዜ የተመቸኝ ደስተኛ እመስላቸዋለሁ እኔ ግን አንድም ቀን ደስ ብሎኝ አያውቅም ሁልጊዜ የሚሰማኝ ባዶነት ነበር የመኖሬ ትርጉምም አይገባኝም እውነት ነው ከፍተኛ ደመወዝ አገኛለሁ ጥሩ እኖራለሁ የምፈልገውን ነገር ማድገግ እችላለሁ ይህ ግን በውስጥ ያለውን እኔነቴን አይገልጥም ነበር።

በዚህ ሁሉ ለዚህን ያህል ዓመት በዚህ ሁኔታ ሳልፍ ግን የምትሰራው ትክክል አይደለም ብሎ አጥብቆ የመከረኝ የለም፤ አባቴ ምንም እንኳን በቅርብ ባይኖርም ሊጠይቀኝ ሲመጣ ሁኔታዬን እያየ ትክክል እንዳልሆነ ይነግረኝ ነበር፤ እኔም ነገሩን ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለሁም ምክንያቱም እንደማልችል ስለማውቅ ነው።

ይህ ህይወት እያንገፈገፈኝ፤ እየመረረኝ መጣ እግዚአብሔር ብቻ ግን ከዚህ ነገር ሊያወጣኝ እንደሚችል ቀድሞም አውቅ ነበር በነበርኩበት ቤተ እምነት ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ከዚህ ህይወት እንዲያወጣኝ በየቦታው ሄጄ ተሰፋ ያለው ነገር ግን ብዙም ሳልርቅ በኃጢያት ሰወድቅ እራሴን አገኛለሁ።

ቀድሞ ከምሰራበት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ከመጣሁ በኋላ ለውጥ ኣሳያለሁ የሚል ግምት ቢኖረኝም ለጥፋት የበለጠ የተመቻቸ ከተማ ገባሁ አዲሱ ሥራዬም ብዙ ጊዜ ወደ መስክ የሚያስወጣኝ ስለነበረ በማያውቁኝ ቦታ ስዘዋወርም ባሰብኝ፤ በዚህ ውስጥ እያለው ባለቤቴ ጌታን ተቀብላ ጴንጤ ሆነች ወትር ስትጸልይ ነው የማገኛት እኔ አምሽቼ ሠክሬ ስገባ እርሷ ተንበርክካ ሳያት እቀናለሁ ምነው እግዚአብሔር ለእኔም ይህን ህይወት ቢሰጠኝ እላለሁ፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሰው እንዳያየኝ ከከተማ ዳር ዳር ወደሉ ጴንጤ ቤተክርስቲያኖች እየሄድኩ ጌታን መቀበል እፈልጋለሁ እያልኩ ብዙ ጊዜ ተጸለየልኝ እኔ ግን በራሴ ላይ ለውጥ አላይም ራሴን ማዘዝ አልችልም፤ አልጠጣም ብዬ ላለመጠጣት አልችልም በግድ ሄጄ እጠጣለሁ፤ ስለዚህ እግዚአብሔርንም ፈልጌው ስላልተቀበለኝ በራሴም መለወጥ ስላልቻልኩ፤ በዚህ ዓይነት ህይወት መቀጠል ደግሞ ስለማልፈልግ መፍትሄው ራሴን ማጥፋት መሆኑን ወሰንኩ።

ባለቤቴና ልጆቼ ለጊዜውም ቢሆን እንዳይቸገሩ ሁኔታዎችን አስተካክልኩ ቀን ወሰንኩ ራሴን ለማጥፋት የምጠቀምበትን መድሃኒት አዘጋጀሁ፤ በወሰንኩበት እለት ከሰዓት በኋላ በዚህ ሃገር 5 ፒኤም ገደማ ባለቤቴንና ልጆቼን በዚያን ጊዜ ትናንሽ ነበሩ ወደ ሳሎን ጠራኋቸው ምንም አለልኳቸውም ዓይን ዓይናቸውን ተመለከትኩ እምባዬ በአይኔ ሞላ እንዲያውቁብኝም ስላልፈለግሁ በእግሬ ከቤት መጣሁ ያለወትሮዬ መኪናዬን አልያዝኩም በታክሲ ተሳፍሬ ድርጊቱን ለመፈጸም ወደ አሰብኩበት ሆቴል ሄድኩ መኝታ ክፍል ተከራየሁ ራሴን ለማጥፋት ያሰብኩበትን መድሃኒት ፊት ለፊት ከአልጋው አጠገብ አስቀመጥኩ ጤነኛ ሆኜ ላደርገው እንደምፈራ ስላወቅሁ ወደ ቡናቤት ገብቼ መጠጣት ጀመርኩ::

ይህ ቡና ቤት ከጓደኞቼ ጋር የምናዘወትርበት ከከተማ ወጣ ያለ ሥፍራ ነበር፤ ሰዎቹም ያቁኛል፤ በዚያን እለት ግን መጠጡንም ቶሎ ቶሎ ነበር የምጠጣው ከዚህም በላይ ደግሞ ለወትሮው ስጠጣ የነበረው ሳቅ ጨዋታ ቀርቶ ብቻዬን መነጋገር ማልቀስ ሆነ ይሄ በቡና ቤቱ ለሚያስተናግዱት እንግዳ ስለሆነባቸው የሆቴሉን ሥራ አስኪያጅ ጠርተውት ኖሮ መጥቶ ወደ ቤቴ እንድሄድ ጠየቀኝ እንደማልሄድ ነገርኩት ወደ ክፍሌም ገብቼ እንድተኛ ጠየቀኝ ፈቃደኛ አልነበርኩም በመጨረሻ ግን በራሴ ጊዜ ወደ መኝታ ክፍሌ ገባሁ ከላይ እንደነገርኳችሁ በፍጹም እንዳልረሳው መድሃኒቱን ከአልጋው አጠገብ አስቀምጬዋለሁ ።

ይቀጥላል........!!!

## የትምህርት ዓምድ

## የእውነተኛ ክርስቲያን ባህሪ

በአንድ ወቅት የአንድ ቤተክርስቲያን መጋቢ የነበሩ ሰው ከምእመናኑ መካከል አንድ ሰው አካሄዱ አነጋገሩ አደራረጉ ሁለተናው ምንም ክርስቲያን አልመሰል ቢላቸው አንተ ሰው ለመሆኑ ክርስትና ገብቶሃል ቢሉት በደንብ ገብቶኛል ብሎ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ጥቅስ እያጣቀሰ መናገር ጀመረ በዚህ ጊዜ ንግግሩን አስቁመው ልጄ ሆይ ሰማኝ ጥቅስ ጥቀስልኝ አላልኩህም ኑሮህ እንደ ክርስቲያን አይደለም ቢሉት እኔን ምን አሳዮት የራሶን ኑሮ ይኑሩ ቢላቸው በንግግሩ በጣም... ልጄ ሆይ ላይህ ፈልጌ ሳይሆን ምኛ ነጭ ሉክ ነን ሳንወድ በግድ እን... በመቅረዝ ላይ ያለ መብራት ሊደበቅ እንደማይችል ሁሉ እኛም እን... አሉት፤ እንግዲህ ስለ እውነተኛ ክርስቲያን ባህሪ ስናስብ መሠረታችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ዙሪያ ምን ያስተምረናል የጻፉትስ ሰዎች እነማን ናቸው እንዲትስ ጻፍት ወደ ፖስተር ምህረቱ መልእክት እንሂድ።

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ዘመናት እና በተለያየ ሞያ ተሰማርተው ይኖሩ የነበሩ ከአርባ የሚበልጡ ሰዎች ናቸው በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የጻፉት። ከጸሐፊዎቹ መካከል ሙሴና ኢያሱ መሪዎች፤ ዳዊት የበግ ጠባቂ የነበረ በኋላም ንጉሥ ፤ አምድ፤ ዋርካ ለቃሚ፤ ዳንኤል የመንግሥት ባለሥልጣን፤ማቴዎስ ቀራጭ፤ሉቃስ ሐኪም፤ ጴጥሮስ ዓሣ አጥማጅ የቀሩትም የተለያየ እውቀትና ሙያ ያላቸው ሰዎች ሆነው ሳሉ ይህ የእግዚአብሔር መለኮታዊ መገለጥ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለክርስቶስ አዳኝነት ከመናገሩ ባሻገር ክርስቲያን የተባለ ሁሉ ማለት በክርስቶስ አዳኝነት በማጤን ዳግመኛ ከመንፈስ በመወለድ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ክርስቲያን በየእለት ህይወቱ ወይም ኑሮው ምን አይነት ባህሪ ሊኖረው እንደሚገባ በስፋትና በጥልቀት ይናገራል እነዚህ ጥቅሶች ሁለቱንም ሃሳብ ያዘሉ ጥቅሶች ናቸው።

ዮሐንስ 20፡31 ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል። ሮሜ 8፡29 ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰኖአል።

እንግዲህ የክርስቲያን ክርስቲያናዊ ባህሪ ምን ሊመስል ይገባል የሚለውን ሃሳብ ከማወቃችን በፊት አስቀድመን ልናውቀው የሚገባን ስለእኛ እውነተኛ የክርስቶስ ኢየሱስ ተከታዮች መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል።

- ቅዱሳን 1ቆሮ 1፡3
- ከማይጠፋ ዘር ዳግመኛ የተወለድን 1ጴጥ 1፡23
- የሰማዩ ጥሪ ተካፋዮች ዕብ 3፡1፤ የዓለም ብርሃን ማቴ 6፡13 ፤ የምድር ጨው ማቴ 6፡13
- የእግዚአብሔር ልጆች 1ዮሐ3፡1፤ ዮሐ 1፡12
- የክርስቶስ ኢየሱስ በጎች ዮሐ 10፡2-7፤ ዮሐ 21፡17
- የኢየሱስ ወዳጆች ዮሐ 14፡14
- የኢየሱስ ወንድሞችና እህቶች ዕብ 2፡13
- የእግዚአብሔር ቤተሰብ ኤፌ 2፡19
- የክርስቶስ አካልና ሙላት ኤፌ 1፡23
- የክርስቶስ ሙሽራ ራዕ 22፡17
- ሕያዋን ድንጋዮች 1ጴጥ 2፡3
- የእግዚአብሔር መልእክተኞች 2ጴጥ 5፡19
- የተለየ ወገን 1ጴጥ 2፡9 ፤የንጉሥ ካህናት 1ጴጥ 2፡9
- የተመረጠ ህዝብ 1ጴጥ 2፡9

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በአብርሃም አማካይነት ለእሥራኤል ህዝብ በገባው የተሰፋ ቃል መሠረት ከ430 ዓመት በኋላ የባርነትን ቀንበር ሰብሮላቸው ሕዝቡን ነፃ አወጣ። የኤርትራንም ባህር ከፍሎ አሻገራቸው፤ የእግዚአብሔር ዓላማ ህዝቡን ነፃ ካወጣ በኋላ እየመራቸው፤ ወተትና ማር ወደምታፈሰው ወደከነአን ምድር ማስገባት ይህ ብቻ ዋነኛ ዓላማው አልነበረም በዘፍ 19፡5-6 እንዲህ ይላቸዋል፤ እውነት ቃሌን ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአህዛብ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ እናንተም የካህናት መንግስት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑሉኛላችሁ ዘሌ 19፡2 እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ዓላማ ነፃ ባወጣው ህዝብ የቅድስናውን ባህሪ መግለጥ ነው። ወደ አዲስ ኪዳንም ስንመጣ የክርስቶስ ኢየሱስ አካል በሆነች ቤተክርስቲያን ወይም ዳግመኛ በተወሰዱ ቅዱሳን እግዚአብሔር በልጁ የራሱን ባህሪ እንደገለጠ ሁሉ በእኛ ደግሞ የክብሩን መንጸባረቅና የባህሪው ምሣሌ የሆነውን የኢየሱስን ክርስቶስን ባህሪ መግለጥ የእግዚአብሔር ዋነኛ ዓላማ ነው።

**መጋቢ ምሕረቱ ለጄቦ**

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን
ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH BOSTON
88 TREMONT STREET, BOSTON, MA, 02108
T: 617-523-5058 F: 617-523-5058
www.eecBoston.org